

# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ
# Ethiopian Civil Service University

**_Public Relations Directorate_**

Monthly Newsletter
March 2017
Vol.13 No.5

## የጥልቅ ተሀድሶ ግምገማ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

የኢትዮጲያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲም ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የአገራችንን ፐብሊክ ሰርቪስ የማስፈጸምና የመፈጸም አቅም በመገንባት በሀገራችን ልማትና መልካም አስተዳደር ግንባታ ሂደት የበኩሉን ድርሻ ሲወጣ የቆየ ቢሆንም ህብረተሰቡን ከሚያማርሩ ማለትም ከኪራይ ሰብሳቢነት፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የጸዳ ሲቪል ሰርቪስ በመገንባቱ ሂደት የሚቀሩ ብዙ ስራዎች እንዳሉ ተስተውሏል:: ከዚህ አንጻር በሲቪል ሰርቪሱ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን ዩኒቨርሲቲውም የሚጋራቸው ናቸው:: እነዚህን ጉድለቶችን በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ እየተካሄደ ባለው የአሥራ አምስት ዓመታት በጥልቀት መታደስ ሂደት በደንብ መፈተሽና እንዲታረሙ የማድረግ ስራ በመስራት ላይ ነው:: በአንድ በኩል ጉድለቶቹን በደንብ መዘርዘርና ከዩኒቨርሲቲው ሁኔታ ጋር እየተፈተሹ የጋራ አቋም የሚወሰድበትን ሁኔታ መፍጠር በሌላ በኩል ደግሞ ጉድለቶችን ለማስተካከል የሚያስችል ግንዛቤና ተነሳሽነትን መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ የጥልቅ ተሀድሰው መድረክ ይህንን ማሳኪያ እንደሚሆን ይታመናል:: በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ





ዩኒቨርሲቲ መላውን ሰራተኛ ያቀፈ የጥልቅ ተሀድሶ ግምገማ ከጥር 15/2009 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ የካቲት 08 2009 ሲያካሂድ ቆይቷል::

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የጥልቅ ተሀድሶ በክፍል አንድ "ብቁና ውጤታማ ፐብሊክ ሰርቪስ ለአገራዊ ሕዳሴ" በሚል የተዘጋጀው ሀገራዊ ሰነድ እና በዩኒቨርሲቲው የስድስት ወር የስራ አፈጻጸም ላይ በቀረበ ገለጻ ላይ ተመስርቶ የተደረገ የቡድን ውይይት፣ በክፍል ሁለት ደግሞ አጠቃላይ የተቋሙ ቁመና እና የከፍተኛና የመካከለኛው አመራር አካላዊ ግምገማ እንዲሁም በክፍል ሶስት የፈጻሚዎች የአካል ግምገማ በመያዝ በሶስት ክፍሎች ተከፍሎ የተከናወነ ነው:: የጥልቅ ተሐድሶው ዓላማም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥትን ባህሪያትና የሚጠበቅበትን ገንቢ ሚና በውል ተገንዝቦ ለላቀ የህዝብ አገልጋይነት እንዲነሳሳ ለማድረግና በዩኒቨርሲቲው የሚስተዋሉ በአስተሳሰብና በተግባር የህዝብ አገልጋይነትና ውጤታማነት የሚጎዱ ዝንባሌዎችን በዴሞክራሲያዊ የሀሳብ ትግል በማስተካከል የቀሪ GTP ሶስት ዓመታት ተግባራትን በላቀ ደረጃ ለመፈጸም የሚያስችል ዝግጁነትና ተነሳሽነት መፍጠር ነው::

በአገራዊ የለውጡ ሂደት ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የማረጋገጥ አቅጣጫ ላይ ግልፅነት እንዲዳብር በማድረግ በአመራሩና በሠራተኛው መካከል ጠንካራ መተማመንና መደጋገፍን መፍጠር፣ በውይይቱ ሂደት ግንባር ቀደሞችንም በመለየት የበለጠ ለማበረታታት እና አደናቃፊ የሆኑትንም በመለየት የተጠያቂነት መርህን ማዕከል በማድረግ አስፈላጊውን ማስተካከያ ማድረግ ነው።

## Our Vision

To become a leading center of excellence in public service capacity building in Africa by 2025 through building efficient, effective, transparent and accountable public service which can contribute to the realization of the development and transformation drive of the country

## Our Mission

Enhancing the service orientation , transparency and accountability of the public service by building its capacity through Specialized Education, Training, Consultancy, Research and Community Services.

## Our Values

- Customer Focus
- Commitment
- Continuous Learning
- Welcoming Diversity
- Attention to the Disadvantaged
- Participatory leadership
- Collaboration

**በክፍል አንድ *የጥልቅ ተሐድሶው መድረክ*** በመጀመሪያ የጥልቅ ተሀድሶውን ፕሮግራም በጥብቅ ዲሲፕሊን ይመራ ዘንድ የበላይ አመራሩ እንዲመራው እና ሌሎች ስራዎችን ኮሚቴዎችን በማቋቋም እንዲከናወን የዝግጅት ምእራፍ መድረክ ከመምራት እስከ ግብአት ማሟላት፣ ተሳትፎ ከማረጋገጥ እስከ አጠቃላይ ፕሮግራሙ ስኬታማ እንዲሆን ድጋፍ ከማድረግ እንዲሁም የዕለት ተዕለት የነበረውን እንቅስቃሴ በመከታተል እና በመገምገም እንዲመራ ተሀድሶው ስኬታማ እንዲሆን የሁሉም ተግባራት አብይ አስፈጻሚ የበላይ አመራሩ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሀይል መድረክ በሚቀርቡ የውይይት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሰራተኛው በቡድን እየተወያየና ሀሳቡን ያለገደብ እያንሸራሸረ ለጥልቅ ተሀድሶው መሳካት የበኩሉን እንዲያበረክት ለማድረግ የቡድን አወያያችና ጸሀፊዎች እንዲመረጡ ተደርጓል፡፡ በመድረኩ ላይ መላው የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ እንደየስራ ሂደታቸዉ በስድስት ቡድኖች ተመድበው በተሀድሶው መድረክ ተሳትፈዋል፡፡ የግምገማ ሂደቱ የቡድን መጠቃቃት እና መከላከል ሳይኖር በነጻነት ሀሳቦች የሚንሸራሸሩበት መሆን አንዳለበት፣ የመድረኩን አስፈላጊነት ተገንዝበን ሰራተኛዉ በሙሉ በዚህ እንዲያልፍ ማድረግ እንደሚጠበቅ፣ ተሀድሶው ወደ ጀመርነዉ ህዳሴ ጉዞ መንደርደሪያ እና ማስፈጸሚያ እንዲሆን አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡

በተጨማሪም ሁሉም ቡድኖች በየቡድኖቻቸው አጠቃላይ ውይይት ካደረጉ በኋላ በየቡድኑ የተነሱ ሀሳቦች በቡድን አወያዮች አማካኝነት በሀይል መድረክ ቀርበዋል፡፡ በውይይቱ መጀመሪያ ቀን ከፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር በተላከው **"ብቁና ውጤታማ ፐብሊክ ሰርቪስ ለአገራዊ ሕዳሴ"** በሚል የተዘጋጀው ሰነድ በሁለት ክፍል ተከፍሎ በተለያዩ ምሁራን ከቀረበ በኋላ በሦስተኛ ደረጃ ላይ የዩኒቨርሲቲውን የ6 ወራት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ መድረኩም የተመራው በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ፐ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ ነበር፡፡

ብቁ እና ዉጤታማ ፐብሊክ ሰርቪስ ለሀገራዊ ህዳሴ በሚለዉ ሰነድ ላይ የመንግስትንና የፐብሊክ ሰርቪሱን ሚና በተመለከተ የሚነሱ አከራካሪ ርእዮተ-ዓለማዊ ጉዳዮች፣ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት በኢትዮጵያ፣ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስታችን ዋና ዋና ባህሪያትና ተልእኮዎች፣ በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥታችን የ15 ዓመታት ጉዞ የተመዘገቡ ዋና ዋና ውጤቶች፣ ፐብሊክ ሰርቪሱ ላለፉት በርካታ ዓመታት ምን እንደሚመስል፣ በፐብሊክ ሰርቪሱ ዘንድ የሚታዩ የአመለካከትና የተግባር ችግሮች (የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር መስፋፋት፣ በትምክህትና ጠባብነት አመለካከት ውስጥ መግባት፣ ፐብሊክ ሰርቪሱ የእምነት ነፃነትን የሚያከብር ገለልተኛ ተቋም መሆኑን መዘንጋት፣ የክህሎት፣ የሙያዊ ብቃትና የሪፎርም መሳሪያዎች አጠቃቀምና አተገባበር ላይ ያሉ ችግሮች፣ የሪፎርም መሳሪያዎች አጠቃቀምና አተገባበር ላይ የሚታይ ዳተኝነት፣ የለውጥ ሠራዊት ግንባታ ሥርዓቱ የአፈፃፀም ጉድለት፣ በየደረጃው የመንግሥት ሠራተኛ የአስተዳደር ህጎችና የአሠራር ሥርዓቶች መጣስ በሚሉ ጉዳዮች ዝርዝር ማብራርያ ቀርበዋል ፡፡

**በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታን በተመለከተም** በውይይቱ ወቅት ከተነሱት ሀሳቦች መካከል ስርዓቱን ወደ መሬት ለማውረድ የሚያስችል መደላድል አልተፈጠረም፤ የስርዓቱ ምንነት በህብረተሰቡ ዘንድ እንዲሰርጽ የፖለቲካ ስራ አልተሰራም፤ አቋራጭ የመበልጸግ አስተሳሰብ (በመንግስት አመራሮች እና በህብረተሰቡ ዘንድ)የበላይነቱን እየያዘ መምጣቱ፣ የአሁኑ ስርዓት የበፊቶቹን ስርዓቶች ችግሮቻቸውን ነቅሶ በማውጣት የጥላቻ ፖለቲካ ላይ ማተኮሩ (የአመለካከት ለውጥ አለማምጣቱ)፣ መንግስት ከጊዜ ወደ ጊዜ የህዝብ አመኔታው እያሽቆለቆለ መምጣቱ፣ የቀና አስተሳሰብ እጦት፣ ከውስጥ ችግሮች ይልቅ በሌሎች አገሮች ችግር አፈታት ላይ መጠመድ፣ የመንግስት አካላት ከችግሮች ራሳቸውን ነጻ ያለማድረግና አርዓያ አለመሆን የሚሉ ሀሳቦች ተነስተዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በተደጋጋሚ በህዝብ ውይይት የተደረገባቸውና የተለዩ ችግሮች ላይ የተወሰደ እርምጃ አለመኖር፣ የመንግስት ጣልቃ ገብነት ገደብ ማጣቱ፣ መንግስት ሌሎች የልማት ተዋንያኖችን (ሲቪክ ማህበራት፣ መያዶች፣ የግል ተቋማትና ህብረተሰቡን) በሚፈለገው ደረጃ አለማካተቱ፣ የልማት ተነሽዎች የካሳ ክፍያ ተመጣጣኝ አለመሆንና በተቃራኒው መንግስት መሬት በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ እየሸጠ መሆኑ፣ መንግስትና ባለሀብቱ በመጣመር ደሀውን ማህበረሰብ እየበደሉ መሆኑ፣ ችግሮችን ወቅቱ በሚጠይቀው የዕውቀት ደረጃ ከመፍታት ይልቅ በተለመደው አሰራር ለመፍታት መሞከር (ለምሳሌ ከከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዞ የሚከሰተውን ኪራይ ሰብሳቢነት)፣ ዘላቂ የሆነ የስራ ዕድል አለመፈጠሩ፣ የልማት ስራው ከመከናወኑ በፊት ልማቱ ሊያስገኝ የሚችለው እና ሊያመጣ የሚችለውን ጉዳት ያለማመዛዘን/ያለማገናዘብ ችግር፣ ሰዎች ሀሳባቸውን በመግለጻቸው ጭቆና እንዲደርስባቸው ማድረግ፣ ትምክህትና ጠባብነት፣ እኛ ብቻ ነን ለኢትዮጵያ የምናስፈልገው የሚል አካሄድ፣ በዜጎች መካከል የሀብት ክፍፍልና ተጠቃሚነት በእኩል ዓይን አለመታየት፣ የኑሮ ውድነትን፣ መንግስት ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ ከሆነ ለምን የዜጎችን የመኖሪያ ቤት ችግር አይቀርፍም? በአሁኑ ሰዓት መንግስትም የፖለቲካ ፓርቲም ኢህአዴግ በሆነበትና የህዝብና መንግስት ንብረት በመንግስትና በግለሰቦች በተያዘበት ሁኔታ እንዴት ጥልቅ ተሐድሶ ማካሄድ ይቻላል? የሚሉና ሌሎችም ልዩ ልዩ ሀሳቦች ተነስተው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

**ፐብሊክ ሰርቪሱን በተመለከተም** በፐብሊክ ሰርቪሱ የሚመደቡ ሰራተኞች መሰፈርት ሙያዊ ብቃትን ወደ ጎን በመተው ፖለቲካ ታማኝነትን ማዕከል ያደረገ መሆኑ፣ አመራሮች ጥፋት ሲገኝባቸው ተገቢውን አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ወደ ሌላ ቦታ አዛውሮ የማሰራት፤ ተጠያቂነት አለመኖር፣ የሀሰት ሪፖርት ባህል እየሆነ መምጣቱ፣ ደንብና ሥርዓትን ያልተከተለ የግዥ እና ክፍያ ስርአት አሰራር መንሰራፋት፣ የተለያዩ ተቋማዊ አሰራር ማስፈጸሚያ መመሪያዎች አለመኖር የሚሉት ሀሳቦች ተነስተዋል፡፡

**በአጠቃላይ በክፍል አንዱ የተሀድሶ መድረክ** የብዝሀነት እና የብሄር ጥያቄ ባለበት ሀገር የልማታዊ እና ዲሞክራሲያዊ መስመር መንግስት መከተሉ ተገቢ መሆኑን፣ በፌደራሊዝም ስርአት መሰረት ራስን በራስ የማስተዳደር መርህ ተገቢ መሆኑ፣ ትምክተኝነት እና ጠባብነት እንደ አስተሳሰብ በግለሰብም ሆነ በቡድን ሊታዩ የሚችሉ ቢሆንም ለኪራይ ሰብሳቢው ዋሻ የመሆን እድላቸው ሰፊ እንደሆነ ሆኖም ትምክተኝነት እና ጠባብነት የየትኛውም ብሄርም ሆነ ብሄረሰብ መገለጫ አድርጎ መውሰድ እንደማይገባ፣ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ርዕዮተ ዓለም መከተላችን ተገቢ ሆኖ ባህርያቱን የሚሸራርፉ አሰራሮች እንዲወገዱና ሚናውን የሚያጎሉ ተቋማት ሊጠናከሩ ይገባቸዋል በሚሉ ነጥቦች ላይ ስምምነት ተደርሷል፡፡

**በክፍል ሁለት የተሀድሶው መድረክ** ተቋሙን ከተቋማዊ የለውጥ መሳሪያዎችና የመልካም አስተዳደር መርሖዎች አፈጻጸም አኳያ፣ ተልኮን በብቃት ከመፈጸም አንጻር፣ ከአመለካከት እና ከሙያ ስነ ምግባር አኳያ የሚገኝበትን ሁኔታ መገምገምና ደረጃ የመስጠት ሁኔታ እንዲሁም ተቋሙን በመምራት ላይ የሚገኘውን የከፍተኛ እና መካከለኛ አመራሩን በጥልቅ ተሀድሶ በመገምገም የስራ አፈጻጸም ደረጃ መስጠት አካሄድን በመከተል ተካሂዷል፡፡

በዚህም መሰረት ዩኒቨርስቲው በተቋማዊ አቋምም፣ በአስተዳደር ምን እደሚመስልና በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ አፈጻጸሙ ምን እንደሚመስል፣ በመገምገም አጠቃላይ የተቋሙ ቁመና ተገምግሟል፡፡ ተልእኮውን ምን ያህል ተወጥቷል፣ የአገልግሎት አሰጣጡስ ምን ይመስላል፣ ተገልጋዮችን ምን ያህል አርክቷል፣ ኪራይ ሰብሳቢነትን ከመዋጋት እና ትምክህተኝነትና ጠባብነትን ከመዋጋት እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ከመገንባት አኳያ እንደ ተቋም ምን ተሰራ ምን ያህልስ ቁርጠኝነቱ አለ ፤ የተቀመጡትን እሴቶች ተግባራዊ ከማድረግ አኳያስ ዩኒቨርስቲው ምን ይመስላል የሚለው በስፋት ተዳሷል፡፡

**የተቋማዊ ለውጥ መሳሪያዎችና የመልካም አስተዳደር መርሆች አፈጻጸም ላይ በተደረገው ውይይት** የለውጡን ስርአት የክትትል ሂደት ቢዘረጋም ሪፖርት በማድረግ ላይ የቆየና ስር የሰደደ ችግር እንዳለ ተጠቅሷል፡፡ በአንደኛው የዝግጅት ምእራፍ የቁልፍ ተግባራት አተገባበር መረጃ በአግባቡ ባለመቅረቡ ሪፖርት አፈጻጸሙ ላይ ከፍተኛ ችግር እንዳለና በተሟላና በተፈለገው መልክ እየሄደ አለመሆኑ ታይቷል፡፡ የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመቅረፍ መመሪያዎችን አስቀምጠን፣ በግልጽ መስራት፣ የአሰራር ስርዓትንና አደረጃጀቶችን፣ ጋይድ ላይን አስቀምጠን ተንቀሳቅሰናል ለሚለው ገና ብዙ ይቀራናል፡፡ ጥርት ያለና የታተመ የዩኒቨርስቲ ሌጅስሌሽን በአካዳሚኩ ዘርፍ አለመኖሩ ተቋሙን ይገልጸዋል፡፡ የመልካም አስተዳደር ችግርን መቅረፍ አልቻልንም፡፡ ከተቋሙ ከሚጠበቀው አንጻር ሲታይ ግን ክህሎት ያላቸውና ለሌሎችም የሚተርፉ አሰልጣኞች በእጃችን እያሉ በዚህ ደረጃ ላይ መገኘታችን በራሱ ችግር ነው፡፡ አርአያ ሆነን መገኘት ሲኖርብን በእዚያ ደረጃ ላይ አይደለንም በሚል ክፍተት መኖሩ ታምኖበታል፡፡

**ተልዕኮን በብቃት በመፈጸም ላይ በተደረገው ውይይትም** ዩኒቨርሲቲው በስትራቴጂክ እቅድ እየተመራ ያለ መሆኑ ተገልጿል፡፡ የስትራቴጂክ ዕቅዳችንን ለመፈጸም ምን ችግር ገጥሞናል የሚለውንም ለማየት እንደተሞከረ ተብራርቷል፡፡ በቀድሞው አሰራር መሪ ዕቅዱ ይዘጋጅና ከዚያ በመነሳት ፈጻሚው ያቅድ ነበር፡፡ ዕቅዱም ትሬሽ ሆልድ አልነበረውም፡፡ በአሁኑ በስትራቴጂክ እቅድ ትሬሽ ሆልድ በማስገባት በቢ ኤስ ሲ በማቀድ መስከረም ላይ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ከስራ ክፍሎች ወጤት ለማስመዝገብ የፕሮግራም በጀት የለንም የሚል ጥያቄ ይነሳ ነበር፡፡ በፕሮግራም በጀት ማቀድ ላይ በአመራሩ አካባቢ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ስልጠና ሰጥተናል፡፡ ዕቅዱ እንዴት ሪፖርት ይደረግ የሚለው ላይ ግን ችግሮች ይታያሉ፡፡ ጥቂት ክፍሎች ወቅቱን ጠብቀው የተሟላ ሪፖርት ሲያቀርቡ አንዳንዶቹ ግን በቢ ኤስ ሲ ያልተፈጸመና በቁጥር ያልተደገፈ የጽሑፍ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡ እቅዶቹ ተያየዥነት ባለው መልክ እንዲወርዱ ቢደረግም ሪፖርቱ በጊዜው በተሟላ መልኩ አይቀርብም፡፡ የተመደበለት በጀትም የታለመለትን ውጤት ማስገኘቱን የሚያስገመግም አይደለም፡፡ ሰልጣኞችም ምን ያህል ለፐብሊክ ሴክተሩን አገልግሎት ተሰጥቷል የሚለውንም የሚያሳይ አሰራር አልነበረም፡፡ ይህም እንደክፍተት ተወስዷል፡፡

ተቋሙ እንደ ተቋም እቅድ አለው ፡፡ ነገር ግን የክልሎችንና የፌዴራል ተቋማትን በሀገር ደረጃ በማሳተፍና ዳሰሳ በማድረግ ፍላጎታቸውነን ለማሟላት የሚያስችል የተሟላ ዕቅድ ማዘጋጀት ላይ የሚቀር ነገር አለ፡፡ በቢኤስ ሲ የለውን ዕቅድ በትክክል ካስኬድ በማድረግ ላይ፣ በተከታታይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ላይ ክፍተት መኖራቸው ታይቷል፡፡ የሶስትና የስድስት ወር ሪፖርት ከማቅረብ ውጪ በየጊዜው ሪፖርት የማድረግ ችግርም አለ፡፡ ተማሪዎችን በማብቃት ፣ በስልጠናና በማማከር የተሰሩ ስራዎች እንዳሉ ሆነው ተልዕኮን በብቃት በመወጣት ረገድ የተለያዩ ክፍተቶች መኖራቸው ተመላክቷል፡፡

**አመለካከትን በተመለከተ** ከኪራይ ሰብሳቢነት ፣ከሙስና ፣ ትምክህተኛነትና ጠባብነት፣ ከሃይማኖት አክራሪነት፣ ከኢ-ዲሞክራሲያዊ አመለካከት ጋር በተያያዘ ዩኒቨረሲቲው እንዴት ይገለጻል የሚለው በስፋት ታይቷል:: ከእነዚህ አመለካከቶች አንጻር በአካዳሚኩም ሆነ በአስተዳደር መዋቅሮች ላይ እንደ ተማሪዎች አገልግሎት፣ ቤተ መጻሕፍት፣ ግዢና ፋይናንስ ሬጂስትራር አካባቢ ፈጣን አገልግሎትን እንዴት እየተሰጠ ነው የሚለው በጥልቀት ተፈትሿል:: ኪራይ ሰብሳቢነት በተቋሙ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ በመምህራን ቅጥር ዙሪያ፣ በወሊሶ ግንባታ፣ በምርምር በጀት አሰጣጥና ወቅቱን ጠብቆ ማወራረድ ላይ፣ በግዢ አካባቢ ይታያሉ የሚባሉ ችግሮች፤ አለአግባብ የመጠቀምና የመጠቃቀም ነገር እንዳለና አድሎአዊ አሰራር መኖሩን ሰዎች ይናገራሉ የሚሉ ጉዳዮች ተነስተው በዝርዝር ታይተዋል:: የሚመለከታቸው የስራ ክፍል ኃላፊዎች በተነሱት ጉዳዮች ላይ ምላሽና ማብራሪያ ሰጠተዋል::

የኪራይ ሰብሳቢነት መገለጫዎችም በርካታ እንደ መሆናቸው መጠን ከሙስና ፣ ከአገልግሎት አሰጣጥ አኳያ ተቋሙ የሚገኝበትን ደረጃ ማየት እንደሚያስፈልግ ታምኖበታል:: ዲሞክራሲን ከማስረፅ አንጻር በተቋሙ በተገቢው ሁኔታ አለመስረጹም ተገልጿል:: በየዘርፉ ያለውም አመራር ላይም የውሳኔ አሰጣጥም ላይ ችግር እንዳለ ተገልጿል::

**በሙያ ስነ ምግባር ዙርያላይ በተደረገ ውይይት** በቡድን ስሜት እየሰራን ነው ወይ? በስነ ምግባራዊ ተግባራት አኳያስ ተቋሙ በምን ደረጃ ላይ እይገኛል? የሚለውን ባለው አደረጃጀት እንደ ዘርፍም እንደክፍልም በጥልቀት ተፈትሿል:: የቡድን ስሜት እንደ ተቋም ለውጤት መትጋት ብዝሃነትን ማክበር፣ እንደተቋም ማስጠበቅ ምን ያህል እንደተሰራበት ታይቷል:: በእነዚህ ጉዳዮች ላይም የተቋሙን ገጽታ ሊያጎድፉ የሚችሉና በጣም የተጋነኑ ነገሮች አለመኖራቸው ተጠቅሷል:: ያለ በቂ ምክንያት ከስራ መቅረት እና የመንግስት የስራ ሰዓት በጥንቃቄ አለመተግበር ችግር ሊስተካከል እንደሚገባው ተነስቷል:: የቡድን ስሜት ከበላይ አመራሩ ከመጣና ጠንካራ ከሆነ ወደታች በየደረጃው ይወርዳል:: በባለቤትነት ስሜት ከተያዘና ሁሉም የድርሻውን ከወሰደን የቡድን መንፈስ ይፈጠራል:: በመተሳሰብና በመደጋገፍ እንደ አንድ የመስራት መንፈስ ይጠነክራል:: ቅንነትና መተሳሰብ ለአንድ አላማ መቆም ይገባል፡ ከሚል ድምዳሜ ላይም ተደርሷል::

**በማጠቃለያው ላይም** ተቋሙ እንደ ተቋም የተጣለበትን ተልዕኮ በመወጣት ላይ መሆኑ፣ ከተቋሙ ተመርቀው የሚወጡ ሰልጣኞች በሀገር ደረጃ እያሳደሩ ያለው ተፅዕኖ ከፍ እያለ የመጣ መኖሩና ዩኒቨርሲቲው በርካታ ጉዳዮች በፖለቲካው ፤ ኢኮኖሚውም ፤ በአመራር ደረጃም ተጽዕኖ ፈጣሪ ተቋም እንድሆነና በክልልም ሆነ በፌደራል ደረጃ ሀገሪቷን እየለወጡ አሁን ካለችበት ደረጃ ያደረሱ አመራሮች በአብዛኛው ከዚህ ዩኒቨርስቲ የወጡ መሆናቸውን የሚታወቅ ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመጣው የመንግስትም ሆነ የማህበረሰቡ ፍላጎትና ከተቋሙ የሚጠብቀው ነገር እጅግ ሰፊ ከመሆኑ የተነሳና ተቋሙም አሁን ባለበት ሁኔታ ያንን ፍላጎት ሙሉ በሙሉ ለማሟላት ባለመቻሉ ተቋሙ እንደ ተቋም በመካከለኛ ደረጃ የስራ አፈጻጸም ደረጃ ላይ ተፈርጇል:: ከዚህ በመቀጠልም ዩኒቨርስቲውን እየመራ ያለው ከፍተኛ አመራር ሂስና ግለ ሂስ በማድርግ በጥልቀት የመታደስ መድረክ ተከናውኗል:: በዚህም መሰረት በአንዳንድ አመራሮች ዘንድ እንደ አመራር የተሟላ እቅድ አዘጋጅቶ በእቅዱ መሰረት አለመመራት ፤ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል አለማድረግ የሚሉት ተጠቃሽ ክፍተቶች ተለይተዋል:: እንደ መሪ ከስሩ ካሉ ሰራተኞች ጋር ተናቦ መስራት ላይ ችግሮች መኖራቸውም የተጠቀሰ ሲሆን ለወደፊትም መታረም እንደሚገባውም ታምኖበታል:: አንዳንድ መጣራት የሚገባቸው ጉዳዮችም በጥልቀት እንዲታዩና እንዲጣሩ አቅጣጫ ተሰጥቷል::

በአካዳሚክ ዘርፉ የኮሌጅ ዲኖችና የትምህርት ክፍል ዳይሬክተሮች ጥልቅ ተሀድሶ ግምገማ ግልጽ የሆነ አቋም መያዝ አስፈላጊ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን በለውጥና መልካም አስተዳደር በመከተል ላይ፣ በኪራይ ሰብሳቢነት በመታገል ላይ ተገቢውን ትኩረት ማድረግ ተገቢ መሆኑ ተገልጿል:: ከሀላፊዎችም ሆነ ከፈጻሚዎች ሰራተኞች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ህግና ደንብን በተከተለ መልኩ ሊሆን ይገባል:: መምህራንንም በእኩል አይን ካለማየትና እኩል የሆነ የክፍለ ጊዜ ድልድል ካለማድረግ መምህራንን የሚከፋበት ሁኔታ መኖር የለበትም የሚለውም አጽንኦት ተሰጥቶታል:: የለውጥ መሳሪያዎችን በአግባቡ በመጠቀም መሻሻል የሚገባው መሆኑና ከምንም በላይ ቁርጠኝነት የሚያስፈልግበት ጊዜ ታምኖበታል ::

**በክፍል ሶስት በተደረገው የፈጻሚዎች ሂስ ግለሂስ መድረክም** በነጻነትና በግልፅኝነት የተካሄደ ሲሆን ሂስ ግለ ሂሱም ዲሞክራሲያዊ እንዲሁም በጥልቀት የተከናወነ ነበር :: እያንዳንዱ ፈጻሚም እራሱ ግለሂሱን ካደረገ በኋላ በአወያዩና በስራ ባልደረቦቹ የስራ ሁኔታው ታይቶ ደረጃ የተሰጠበት ሂደትን የተከተለ ነበር:: በተጨማሪም የደረጃ አሰጣጡ አስተማሪ እና መረጃን መሰረት ባደረገ መልክ እንዲሆን ጥረት ተደርጓል ::

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የመምህራንና ሰራተኞችን የጥልቅ ተሀድሶ ግምገማ መድረክን ለማሳካት ያስቀመጣቸውን ዓላማዎችንና ግቦችን በአግባቡ ያሳካ ሲሆን በተለይ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥትን ባህሪያትና የሚጠበቅባቸውን ገንቢ ሚና በውል ተገንዝበው ለላቀ የህዝብ አገልጋይነት እንዲነሳሱ ለማድረግ እና በዩኒቨርሲቲው የሚስተዋሉ በአስተሳሰብና በተግባር የህዝብ አገልጋይነትና ውጤታማነትን የሚጎዱ ዝንባሌዎችን በዴሞክራሲያዊ የኃሳብ ትግል በማስተካከል የቀሪ GTP II ዓመታት ተግባራትን በላቀ ደረጃ እንዲፈፅሙ የሚያስችል ዝግጁነትና ተነሳሽነት ለመፍጠር ተችሏል :: በዩንቨርስቲዉ የተካሄደዉ ጥልቅ ተሀድሶ የተቋሙን ማህበረሰብ ለላቀ የህዝብ አገልጋይነት ከማነሳሳቱም ባሻገር ዝግጁነትና ተነሳሽነትን ፈጥሯል:: በሌላም በኩል በአመራሩና በሠራተኛው መካከል ጠንካራ መተማመንና መደጋገፍን እንዲሁም የተጠያቂነትን መንፈስ አዳብሯል::

# Ethiopian Civil Service University Graduates Students

Ethiopian Civil Service University graduated 258 students with Masters and Bachelor degrees on March 4, 2017 at Abay Hall.





On the graduation ceremony His Excellency Ato Tagesse chaffo Minister for Ministry of Public Service and Human Resource Development said Ethiopian Civil Service University has enormously contributed in building the capacity of the civil servants and over all structural development of the civil service sector for the last two decades. In addition to enhancing the development of the civil service of our country, ECSU is also striving to contribute to build the capacity of



the neighboring countries by training their civil servants. In doing so it enables our country to have a good relationship with East African countries, Ato Tagesse Chaffo added. He also reminded the graduates that the government has conducted deep renewal forums across the county to address the demand of the society and he requested them to exert their utmost efforts by combating mal administration, rent seeking activities and corruption to realize the desired changes.

Finally Ato Tagesse Chaffo thanked the university community for exerting their relentless effort in teaching and giving trainings for the civil servants and urged to further strengthen its effort in the future.

Professor Fikre Dessalegn Ethiopian Civil Service University president on his part congratulated the graduating students for their efforts. He said that Ethiopian Civil Service University has trained and graduated more than 28000 civil servants in the last two decades. It has also given short term training and



consultancy for more than 50,000 participants. Besides, ECSU is also trying to work hard to reform the public sectors by conducting researches in its research and community service wing and benefited the local community from it. In his message, Professor Fikre Dessalegn encouraged the graduates to put in practice what they have gained during their stay at the university and serve the community and their country at large.

On the occasion Ato Tagesse Chaffo handed out degrees and awards to the graduates and different entertainment programs were presented to the audience.

Ethiopian Civil Service University is now providing trainings to over 3000 students in six PHD, twenty five masters and eight first degree programs. Currently it trains about two hundred students recruited from East African country.

# Ministry of Foreign Affair Holds Graduation Ceremony for Graduating Diplomats

Ethiopian Ministry of Foreign Affair holds Graduation Ceremony for First and Second Round Trainees who are trained in collaboration with Ethiopian Civil Service University on March 11, 2017 at Capital Hotel.




On the ceremony Dr. Workineh Gebeyehu Minister for Ministry of Foreign Affairs congratulated the graduating diplomats. Dr. Workineh Gebeyehu in the occasion said the second growth and transformation program in socio economic transformation is well underway throughout the country. In our diplomatic career we should tell the truth of our country to the world and accurately communicate our image with the external community. Our county expects great efforts from the graduating diplomats he added. He also advised the graduates to update themselves, diversify their knowledge and fully discharge the role of diplomats in this complicated world. He also thanked the Ethiopian Civil Service University for its contribution in building the capacity of the ministry and the public service in training, research, and consultancy and community service.

Professor Fikre Dessalegn Ethiopian Civil Service University president on his part congratulated the graduates for their successful achievements. He also mentioned that the Ethiopian Civil Service University is closely working with




Ethiopian Ministry of Foreign Affair, Ministry of Urban Development and Ethiopian Custom and Revenue Authority by launching demand based programs. ECSU and Ministry of Foreign Affair work together to bridge the gaps and produce skilled professionals in the diplomatic areas. In the last six years, more than ninety diplomats have been trained through short term training programs and post graduation programs Professor Fikre Dessalegn said. He also conveyed his message to the graduates to try their level best to promote and strengthen the relationship of our country with external community and increase their level of competence in the diplomatic arena.
On the occasion His excellence Dr. Workineh Gebeyehu handed over diplomas for the graduates



and certificates of recognition for different institutions, organizations, scholars and diplomatic communities who have contributed in the training programs.

It is o be recalled that the Ethiopian Civil Service University has also graduated more than two hundred and fifty students including graduating diplomats on March 4, 2017 at Abay Hall.

## Ethiopian Civil Service University and Ethiopian Kaizen Institute Sign Cooperation Agreement

Ethiopian Civil Service University and Ethiopian Kaizen Institute signed a mutual Cooperative Agreement on March 16, 2017 at Hidasse Hall in the presence of the Institutions Higher managements. On the occasion first level Kaizen philosophy application program has been declared in Ethiopian Civil Service University.



After the signing of the agreement professor Fikre Dessalegn Ethiopian Civil Service University President said we have laid the foundation for our future activities by giving continuous trainings to our staffs by Kaizen institute. Having this knowledge, we have now started practicing Kaizen philosophy at the university level. For this, the front liner should work harder than ever to put into practice what you gained from the trainings. Use the available resources and make the environment suitable for work and bring an overall transformation in the university, professor Fikre Dessalegn said. He also added that kaizen is a continuous process and the result of today's activity has its own impact on future development. Being pioneer you should bring a sustainable transformation in our institution. I can affirm you that the management of the university stand by your side in your activities and give recognition to the best performers, he underscored.

On his part, Ato MekonenYahi, Kaizen Institute Director said since its introduction to our country, kaizen has been practiced in both industrial and service giver sectors and brought changes at all levels. Taking these good experiences as basement, the Ethiopian Civil Service University today started the kaizen practice at institutional



level.Ethiopian Kaizen Institutecontinuously give its assistance to the university in its activities, Ato Mekonen said. We are working to have our own working and leadership philosophy in harmony with our culture and living styles at national level. For this we hope that the Ethiopian Civil Service University will contribute in its full capacity, he added.



In his report Ato AyneabebaAndualem , ECSU Reform and Good Governance OfficeDirector pointed out that in accordance with our agreement, Ethiopian Kaizen Institute trained the Directors and more than two hundred staff members. To make our University center of excellence and to facilitate the growth and transformation program we need to apply kaizen philosophy. For this we now started kaizen in six Directorates of the University. In thenear future I firmly believe that we will make it our work culture he added.

## Centers Hold Research Validation Workshops

Ethiopian Civil Service University Center for Ethics and Integrity and Centre for Research in Public Service Reform organized one day research validation workshop with stakeholders on March 23, 2017 at Hidasse Hall. The research validation workshop was conducted under the theme of Public Service Reform Implementation, Public Service Leadership Ethics and Public Perception on Corruption and Corrupt Practices.



In his opening speech Ato Birhanu Belayneh Ethiopian Civil Service University Research and Community Service Vice President said Ethiopian Civil Service University played its role in overall growth and development of the country for the last twenty five years. It builds the capacity of the public servants through education and bridging the gaps in skills and knowledge by short term trainings. Besides, ECSU, cognizant of the need to intensify research and community service, has been extending its contribution in the area by establishing research and community service wing starting from 2015. Since its establishment it has been working hard in coordinating more than ninety researches which focused on the issues of the public service. The researches have been conducted by individual researchers and research teams, Ato Birhanu Blayneh said. He in the occasion thanked the research teams, the stakeholders and the participants of the workshop and requested them to use the research findings as inputs in their future activities.



On the workshop three research papers entitled The Effect of Public Service Reform in Improving the Quality of Public Service Delivery in Addis Ababa City, Assessment of Public Perception on Corruption and Corrupt practices, and Practice and Challenges of Exercising Ethical Leadership in The Ethiopian Public Sector, were presented by three research teams for validation and the participants have conducted in-depth evaluation on each paper and forwarded their comments and suggestion on the research methodologies and findings.



The research papers presented for validation were conducted by the demand and request of the Ministry of Public Service and Human Resource Development, Federal Ethics and Anti Corruption Commission and Addis Ababa City Administration and have been jointly conducted by ECSU Center for Ethics and Integrity and Centre for Research in Public Service Reform. On the program ECSU higher administrations, invited guests, scholars and stakeholders have participated.